

የኢትዮጵያ አርክቴክቶች ማህበር

ASSOCIATION OF ETHIOPIAN ARCHITECTS

2018

የኢትዮጵያ አርክቴክቶች ማሕበር

የስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ የ2018 ዓ.ም.

አመታዊ የስራ ክንውን ሪፖርት

የኢትዮጵያ አርክቴክቶች ማሕበር ስራ አስፈጻሚ

ጥቅምት 21 2019 ዓ.ም.

ኢአማ
AEA

ማጠቃለያ ሪፖርት

አዲሱ የስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ከተመረጠበት ታሕሳስ ፲፩ ቀን 2018 ዓም ላለፉት ፲0 ወራት ብዙ ስራዎችን ሲሰራ ቆይቷል። ከማኔጅመንቱ የጋራ ስብሰባዎችን በተከታታይ በማድረግ ለማሕበሩ የእለት ተእለት ተግባራት እና በሙያው እና ባለሙያው ላይ ለውጥ ሊያመጡ ይችላሉ ያላቸውን እቅዶች በማውጣት እና ወደ ትግበራ በመግባት ከፍተኛ እንቅስቃሴዎችን ሲያደርግ ቆይቷል። በዚህም በብዙ ቦታዎች ላይ ታላላቅ ለውጦችን ማስመዝገብ የቻለ ሲሆን በተለይም ደግሞ የማሕበሩን ውስጣዊ አደረጃጀት ከማዘመን፣ የማሕበሩን ገቢ ከማሳደግ፣ አለማቀፋዊ ግንኙነቶችን ከማስቀጠል እና ሙያውን እና ባለሙያውን በመወከል ረገድ እጅግ አመርቂ ስራ ሰርቷል። በሌላ በኩል የአባላትን ተሳትፎ ከማረጋገጥ እና እንደ አርክቴክትስ ወርሃዊ የመሰሉ ኩነቶችን በዘላቂነት ከማስኬድ አንጻር ደካማ አፈጻጸም አሳይቷል።

ስራ አስፈጻሚው ያሉትን በጎ ስራዎች በማስቀጠል ደካማ አፈጻጸም የታየባቸውን ደግሞ አሻሽሎ ለመገኘት ይረዳኛል ያለውን የሁለተኛ አመት የስራ እቅድ አውጥቷል። ይህም በዚሁ ሪፖርት ተያይዟል። ማሕበራችን ዘንድሮ 35ኛ አመቱን እንደማክበሩ፣ ባለፉት 35 አመታት በትውልድ ቅብብሎሽ በርካታ ስራዎችን ከውኗል። የዛሬውም ስራ አስፈጻሚ ያለፉት በተውለት ቅሪት ላይ ተነስቶ ለነገው አመራር የሚሆነ የቁርሾ ስራ እንደሚሰራ ስለሚያምን፣ በተቻለው መጠን ሌሎች ስራዎች እንዳሉ ሆነው ዘመኑን የዋጀ የዳታ ማኔጅመንት እና የሙያ ሕግ ላይ አበርትቶ ለመስራት ታላቅ ዝግጅት እያደረገ ይገኛል።

በመሆኑም ማንኛውም አባል የማሕበሩን የአባልነት መዋጮ ከመክፈል ግዴታ ባሻገር ጠለቅ ብሎ ማህበሩ በሚያዘጋጃቸ ክንውኖች በምካፈል፣ ከማሕበሩ በሚመጡ የስልጠና እና መሰል እድሎች በመጠቀም እና ሌሎች አባል ያልሆኑ የሙያ አጋሮቻችንን እና አዳዲድ ምሩቃንን ማሕበሩን እንዲቀላቀሉ በመጋበዝ የራሱን እና የወል ሃላፊነቱን ሊወጣ ይገባል እንላለን። ይህ ሪፖርት በ2018 በጀት አመት የተከናወኑ ስራዎችን የሚዳስስ ሲሆነ ከዚህም በተጨማሪ የእነዚህን ስራዎች ግምገማ እና ቀጣይ ሊሰራባቸው የታቀዱ ስራዎችን የያዘ በመሆኑ ማንኛውም አባል በጥንቃቄ አንብቦ አስተያየት በመስጠት ለስራችን መሻሻል ይረዳን ዘንድ ከወዲሁ ልመናችንን እናቀርባለን።

ስራ አስፈጻሚ ኮሚቴው

ኢአማ
AEA

1. መግቢያ

የኢትዮጵያ አርክቴክቶች ማሕበር በታሕሳስ 10 እና 11 ቀን 2018 ዓ.ም. በኢሊሊ ሆቴል ባደረገው የ25ኛው ጠቅላላ ጉባኤ ከቀድሞ አመራሮች እና አዳዲስ አባላትን ያካተተ አዲስ ስራ አስፈጻሚ መምረጡ የሚታወስ ነው። በዚሁ በተደረገው ምርጫ ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ተመራጭ ስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባላት እና የማሕበሩ ማኔጅመንት በጋራ በመሆን የትውውቅ መድረክ ያደረጉ ሲሆን በቀጣይም የጋራ እቅድ ለመንደፍ የሚያስችላቸውን የሁለት ቀናት የጋራ ወርክሾፕ አዘጋጅተዋል። በዚሁም መሰረት ለማሕበሩ እና ለሙያው ቀጣይ እድገት ያግዛሉ ያሏቸውን አንኳር ጉዳዮችን የለዩ ሲሆን ይህ ሪፖርት በበጀት አመቱ የስራ አስፈጻሚው ሊሰራ ያቀዳቸውን እቅዶች አፈጻጸም እና በአጠቃላይ ያከናወናቸውን ክንውኖች የያዘ ሪፖርት ነው።

1.1. የስራ አስፈጻሚ አባላት

1.	ሀብታሙ ጌታቸው	ፕሬዝዳንት
2.	ራሔል ለማ	ም/ፕሬዝዳንት
3.	ዶ/ር ነብዩ ዮናስ	ጸሐፊ
4.	ናትናኤል መስፍን	ም/ጸሐፊ እና የኢቲክስ ክፍል ሃላፊ
5.	በእምነት ደምሴ	ሒሳብ ሹም እና የአባላት ክፍል ሃላፊ
6.	ሴማዊት አየለ	ገንዘብ ያዥ እና የኮምፒቲሽን እና ኤግዚቢሽን ክፍል ሃላፊ
7.	መጥምቁ ዮሐንስ	የሕትመት እና ሰነድ ክፍል ሃላፊ

1.2. የማኔጅመንት አባላት

1.	ሙሴ ግዛው	ዳይሬክተር
2.	ሃና	አካውንታንት

ይህ የስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ እና የማኔጅመንት አባላት በጋራ በአጠቃላይ ሙሉ ቀን የፈጁ ሁለት ጊዜ የእቅድ ዝግጅት ልዩ ስብሰባዎችን ሲያደርግ 12 የፊት ለፊት፣ ስምንት የድሕረ ገጽ፣ እንዲሁም አንድ አስቸኳይ በድምሩ 21 የመደበኛ ስብሰባዎችን በማድረግ ማሕበሩ የእለት ተእለት ተግባራቱ እና በሚያዝጋጃቸው ዝግጅቶች ዙሪያ መክሯል። ከዚህም በተጨማሪ በቁጥር ሊገለጹ የማይችሉ ሕዝባዊ እና መንግስታዊ ስብሰባዎችን የተካፋለ ሲሆን በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የግንባታ ፈቃድ እና ቁጥጥር ባለስልጣን፣ በአዲስ አበባ ከተማ ፕላን እና ልማት ቢሮ እንዲሁም በኮንስትራክሽን ኤክሰለንስ ኢኒሼቲቭ በቋሚነት በመሰለፍ ሙያውን በሚመለከቱ ጉዳዮች ላይ ግብአት በመስጠት የነቃ ተሳትፎ አድርጓል። ከዚህም በተጨማሪ ለአማካሪዎች ሊከፈል በሚገባው አነስተኛ ክፍያ ማኑዋልን ከሌሎች የሙያ ማሕበራት ጋር በመሆን እንዲወጣ ያደረገ ሲሆን በቅርቡም ወደ ስራ እንደሚገባ ባለሙሉ ተስፋ ነው።

2. የተዘጋጁ እቅዶች

2.1. ውስጣዊ አደረጃጀትን ማጠናከር

ስራ አስፈጻሚው የማሕበሩን ውስጣዊ አደረጃጀት ከማዘመን አንጻር የጀመራቸውን ስራዎች በማስቀጠል፣ ይሆናሉ ያላቸውን ተጨማሪ ስራዎችን ሰርቷል። ለመጥቀስ ያህል

- ✓ በየጊዜው የሚጨምረውን የቢሮ ኪራይ ተቋቁሞ ማሕበሩ አሁን ያለበትን የከተማው እንብርት ላይ የሚገኘውን ቢሮውን ጠብቆ እንዲዘልቅ አድርጓል።
- ✓ የቢሮውን የውስጥ ይዘት ለእይታ ማራኪ በማድረግ ለጎብኝዎች የሚስብ ቢሮ እንዲኖረው አድርጓል
- ✓ የራሱ ከለር ፕሪንተር በመግዛት በየእለቱ የሚወጣውን የህትመት ወጭ እንዲቀንስ ከማድረጉም በላይ የማሕበሩ ደብዳቤዎች እና ሰነዶች ጥራት እንዲጠበቅ አድርጓል
- ✓

2.2. የአባላት ተሳትፎን ማጠናከር

ምንም እንኳን እንደተፈለገው ባይሄድም ስራ አስፈጻሚው ስራዬ ብሎ አባላትን በስልክ እና በኢሜይል አባልነታቸውን እንዲያድሱ የጎተጎተ ሲሆን፣ በአብዛኛው ምላሽ ሳያገኝ ቀርቷል። ከዚህ በታች ያለው ሰንጠረዥ በአሁኑ ወቅት ማሕበሩ ያሉትን እና ንቁ ተሳትፎ የሚያደርጉ አባላትን ዝርዝር የያዘ ነው።

Category	Month			
	JAN	APRIL	AUG	OCT
Student	50	67	80	85
GAR	57	60	79	82
PAR	21	22	26	28
PPAR	61	63	63	60
FIRMS	25	25	35	54
Affiliate	1	7	7	7
TOTAL	219	244	290	316

እንግዲህ ማኔጅመንቱ የስራ መርሃግብር አውጥቶ በአራት ክፍለ ጊዜ አባላትን መረጃ ለማድረስ ቢሞክርም ምላሽ የሰጡ አባላት 316 ብቻ ናቸው። ከዚህም በተጨማሪ ማሕበሩ በግንባታ ደሕንነት፣ በፕሮጀክት ማኔጅመንት እንዲሁም በቢም ስልጠናዎች አባላቱ እድል አመቻችቶ ጥሪ ያደረገ ቢሆንም ከጥቂት አባላት በቀር እድሉን ለመጠቀም አልተቻለም። በመሆኑም አሁንም አባላቱ ከፍተኛ የሆነ ተሳትፎ ማድረግ እንደሚጠበቅበት ከወዲሁ ለማሳወቅ እንወዳለን።

የአባላትን ተሳትፎ ከማጠናከር አንጻር በቀጣይ ሊሰሩ የታቀዱ ስራዎች

- ✓ የአባላት ልየታ፣ ምዝገባ፣ ክፍያ እና ምዘና በዲጂታል ፕላትፎርም እንዲሰሩ በማድረግ ምቹ ማድረግ
- ✓ አባላትን የሚያሳትፉ ተጨማሪ ኩነቶችን በማስተናገድ አባላትን ወደ ማሕበሩ እንዲመጡ ማድረግ
- ✓ የከፍተኛ ትምሕርት ተቋማትን በማስተባበር የአዲስ አባላት ብዛትን መጨመር
- ✓ አባላት ምዝገባቸውን እንዲያደርጉ ቅስቀሳዎችን ማድረግ

2.3. የአርክቴክትስ ወርሃዊን ማስቀጠል

ማሕበሩ ባለፈው አመት ሁለት የአርክቴክትስ ወርሃዊ ፕሮግራሞችን ብቻ ነው ያቀረበው። ይህ ከዚህ ቀደም ከነበሩት ዝቅተኛው ቢሆንም፣ በሌላ በኩል ከዚህ ቀደም ይቀርቡ የነበሩት ፕሮግራሞችን ይዘታቸው እንደገና እንዲቃኝ የተሞከረበት እና ጥሩ ውጤት የተገኘበት በመሆኑ ስራ አስፈጻሚው እንዲገፋበት የሚያበረታታ ሆነው ተገኝተዋል። በሌላ በኩል በተለይ ይህ ዝግጅት የአጭር ጊዜ በመሆኑ እና በቦታውም የሚታደሙት በአብዛኛው ወጣት እና ጀማሪ አርክቴክቶች በመሆናቸው ስፖንሰር በማፈላለጉ ሂደት ከፍተኛ ተግዳሮት ገጥሞታል። በመሆኑም የተደረጉት ሁለቱም ፕሮግራሞች በራሱ በማሕበሩ ሙሉ ወጭ የተደረጉ ሲሆን ለመቀጠልም አስቸጋሪ አድርጎታል። በመሆኑም ወደፊት ይዘታቸውን ለሌሎች ሲኒየር አርክቴክቶች እና የስቱዲዮ ባለቤቶች ሳቢ በማድረግ ስፖንሰሮችን የማሳመን ስራ ለመስራት እንደ እቅድ ተይዟል።

2.4. የማሕበሩን ውክልና እና ተደራሽነት ማሳደግ

ስራ አስፈጻሚ ኮሚቴው የማሕበሩን ውክልና በማጠናከር ረገድ እንደማንኛውም ጊዜ ባሳለፍነው አመትም ከፍተኛ ሚናውን ተጫውቷል። ማሕበሩ መንግስታዊ እና መንግስታዊ ባልሆኑ ተቋማት ላይ በመገኘት የሙያውን እና የባለሙያውን ጥቅም ሊያስጠብቁ የሚችሉ ሃሳቦችን አንጸባርቋል። ማሕበሩን እና አባላቱን ሊጎዱ ይችሉ የነበሩ አንዳንድ ረቂቅ የሕግ ማእቀፎች እና አሰራሮች ላይ ጠንካራ አቋሙን በመግለጽ እንዲስተካከሉ ወይም እንዲቀሩ አድርጓል።

በተለይም ደግሞ ማሕበሩ ከሌሎች አጋር ሙያ ማሕበራት ጋር በመጣመር ዝቅተኛውን የአማካሪ ክፍያ መስፈርት ለመወሰን የሚያስችል ረቂቅ ማኑዋልን ከሌሎች ማሕበራት ጋር በመሆን በባለስልጣን መስሪያቤቱ እንዲጸድቅ አድርጓል።

በቀጣይም ማሕበሩ ከታች በተዘረዘሩት ግቦች ላይ በምስራት ውክልናው እና ተደራሽነቱ እንዲጠናከር ይሰራል።

- ✓ ከሚመለከታቸው መንግስታዊ ተቋማት ጋር በቅርበት እና በትብብር መስራት
- ✓ የአርክቴክቶች የሕግ ማእቀፍ ረቂቅን ለባለድርሻ አካላት ማስተዋወቅ እና ተግባራዊ እንዲሆን መጣር
- ✓ መንግስታዊ ካልሆኑ ሙያው የሚመለከታቸው ተቋማት ጋር በጋራ መስራት

2.5. ገቢን ማሳደግ

አዲሱ ስራ አስፈጻሚ ካለፈው የቀጠለውን የማሕበሩን ገቢ በማሳደግ ረገድ ከፍተኛ ጥረትን በማድረግ ላይ ነው። በዚሁም በምናይበት ወቅት ማሕበሩ

ኢአማ
AEA

	2018	2017	2016	2015
Total collected	5,097,981.20	2,283,470.00	1,418,450.97	1,362,431.00
Membership fee	282,320.00	99,770.00	105,170.97	88,231.00
Honorarium Collection	2,195,661.00	564,700.00	345,400.00	499,000.00
Donations	0	70,000.00	10,000.00	4,400.00
Sponsorship	2,620,000.00	1,536,000.00	948,880	450,000.00



ከላይ እንደሚታየው ባለፈው የበጀት አመት ማሕበሩ በጠቅላላው ብር 5,097,981.20 ገቢ መሰብሰብ የቻለ ሲሆን ይህም በታሪኩ ከሰበሰባቸው ገንዘቦች ከፍተኛ የሚሆን ነው። ይሁን እንጂ ይህ ገንዘብ የተሰበሰበው በአብዛኛው ከፖንሰር ሺፕ እና ከተለያዩ ስራዎች የተገኘ እንጂ የአባላት መዋጮን ብንመለከት አሁንም አጥጋቢ አይደለም። በዚሁ አመት የተሰበሰበው ብር 282,320.00 የአባላት መዋጮ እድገት ቢያሳይም ማሕበሩ ካሉት የአባላት ቁጥር አንጻር እጅግ አነስተኛ በመሆኑ በቀጣይ ማሕበሩን ጥቅም ለአንዴ ብቻ በሚፈልጉበት ወቅት የአመቱን ከፍያ ከፍለው የሚመጡ አባላትን የሚለይበት ዘላቂ ስራ በመስራት ላይ ይገኛል። የጠቅላላ የማሕበሩን ኦዲት ሪፖርት ከዚህ ሪፖርት ጋር አባሪ በማድረግ ተያይዟል።

2.6. አለማቀፍ ግንኙነቶችን ማጠናከር

ይህ አመት ማሕበራችን በአለም አቀፎቹ የአርክቴክቶች ማሕበር እና በአፍሪካው የአርክቴክቶች ማሕበር ውስጥ ያለውን ውክልና ለማስቀጠል ከፍተኛ ትግል ያደረገበትም አመት ነበር። በተለይም ከኮቪድ ጀምሮ ባልተከፈሉ የአባልነት ውዝፍ መዋጮዎች ምክንያት እስከ አባልነቱን የማጣት አደጋ ተጋርጦበት የነበረ ቢሆንም፣ ስራ አስፈጻሚው ባደረገው ብርቱ ትግል ከአለም አቀፉ አርክቴክቶች ማሕበር ጋር የተወሰነው እዳው እንዲሰረዝ እና ቀሪው ደግሞ ለረጅም አመት ክፍያ ተሰባጥሮ እንዲከፈል ስምምነት ደርሷል። በዚሁም የኢንተርናሽናል አካውንት በመክፈት በንግድ ባንክ የመጀመሪያውን የአባልነት ክፍያ እስከ ለአመቱ የሚደርሰው 50% እዳ ማካካሻ ክፍሎ ሙሉ አባልነቱን አስጠብቋል። ከዚሁ በተያያዘ ከአፍሪካ አርክቴክቶች ሕብረትም ጋር ተመሳሳይ ስምምነት ላይ ለመድረስ ውይይት ላይ ይገኛል።

በሌላ በኩል በአዲስ አበባ ከሚገኙ አለም አቀፍ ተቋማት ጋር ግንኙነቱን አጠናክሮ የቀጠለ ሲሆን በዚህም ከኤምባሲዎች (ጣሊያን፣ ፈረንሳይ፣ እና ኔዘርላንድ) ጋር እንዲሁም እነ UNICEF እና UNESCO ከመሳሰሉት ተቋማትም ጋር ተከታታይ ግንኙነቶችን በመፍጠር የተለያዩ የትብብር ስራዎችን በመስራት ላይ ይገኛል።

3. የእቅዶች አፈጻጸም እና ግምገማ

የማሕበሩ ስራ አስፈጻሚ እና ማኔጅመንት በተቻለው መጠን የማሕበሩ አንኳር ጉዳዬች ላይ ብዙ ስራ ሰርቷል። ይህንንም ራሱ በየጊዜው በመገምገም ማጠናከር ያለበትን እያጠናከረ የደከመበት ቦታዎች ላይ ደግሞ ምክንያታቸውን ተረድቶ የተሻለ ስራ ለመስራት የሚያስችለውን እቅድ ያወጣል። ከዚህ በታች የሰፈረው ሰንጠረዥ የማሕበሩን የውስጥ ግምገማ የሚመለከት ሲሆን እንደሚታየው በአማካይ **83.99%** ክንውን ፈጽሟል።

የታቀዱ ስራዎች	**የውስጥ ግምገማ**
ውስጣዊ አደረጃጀትን ማጠናከርን በተመለከተ	**95.00%**
የአባላት ተሳትፎን ማጠናከር	**67.61%**
የአርክቴክትስ ወርሃዊን ማስቀጠል	**33.33%**
የማሕበሩን ውክልና እና ተደራሽነት ማሳደግ	**100.00%**
ገቢን ማሳደግ	**100.00%**
አለማቀፍ ግንኙነቶችን ማጠናከር	**100.00%**
የአማካሪዎች ክፍያ	**100.00%**
የአርክቴክቶች የሕግ ማእቀፍ	**85.00%**
የመተዳደሪያ ደንብ የማሻሻል ስራ	**75.00%**
አማካይ	**83.99%**

ኢአማ
AEA

4. ያጋጠሙ በጎ እድሎች እና ተግዳሮቶች

ስራ አስፈጻሚው ባለፈው አንድ አመት በተጓዘቸው ሂደቶች በጎ የሆኑ እድሎች እና አንዳንድ ተግዳሮቶችን ያሳለፈ ሲሆን በተቻለው መጠን ከበጎ እድሎቹ ተጠቅሞ ተግዳሮቶቹን ተቋቁሞ ብቁ አፈጻጸም አሳይቷል

4.1. በጎ እድሎች

- ማሕበሩ ከሌሎች ማሕበራት ጋር ያገኘውን የአማካሪዎች ክፍያ ማኑዋል ላይ የመስራት እድል ተጠቅሞ የማሕበሩን የጸደቀ ክፍያ ማኑዋል መነሻ በማድረግ እንዲሰራ አስችሏል።
- ከመንግስታዊ ባለድርሻ አካላት ጋር የቀረቡለትን ጥሪ ተቀብሎ ሙያውን እና ባለሙያውን ጥቅም ሊያስጠብቁ በሚችሉ ጉዳዮች ላይ ጥብቅና መቆም ችሏል።
- በተለይም ከአዲስ አበባ ግንባታ ፈቃድ እና ቁጥጥር ባለስልጣን እንዲሁም ከኮንስትራክሽን ማኔጅመንት ኢንስቲቲዩት ጋር በመተባበር የተለያዩ ስልጠናዎችን ለአባላት እንዲሰጡ አመቻችቷል።

4.2. ተግዳሮቶች

- የአባላት መዋጮ ማነስ፣ የቢሮ ኪራይ፣ የአገልግሎቶች እና እቃዎች ዋጋ መናር አሁንም ማሕበሩን የሚታገለው ኢኮኖሚያዊ ችግር ነው
- አሁንም ቢሆን አባላት የሚመጡላቸውን እድሎች ከመጠቀም አንጻር ቸልተኝነት በመኖሩ ምክንያት እድሉን በሚሰጡን አካላት ዘንድ ጥያቄ እያጫረብን ተቸግረናል
- በውጭ ገንዘብ ክፍያ መክፈል በጣም አስቸጋሪ ቢሆንም ከአሰልቺ ጉዞ በኋላ መፈጸም ተችሏል

5.

6. በቀጣይ ለመስራት የተዘጋጁ እቅዶች

እቅድ	መለኪያ	ብዛት
1.1. ውስጣዊ አደረጃጀትን ማጠናከርን በተመለከተ		
ጠረጴዛ	በቁጥር	4
ወንበር	በቁጥር	8
ድረ ገጽ ማሻሻል ስራ	በፐርሰንት	100
ዲጂታል ሲስተም	በፐርሰንት	100
1.2. የአባላት ተሳትፎን ማጠናከር		
ዲጂታል ምዝገባ እና ዳታ ቤዝ	በፐርሰንት	100
ቅስቀሳ	በቁጥር	4
የአክቲቭ አባላት ቁጥርን ማሳደግ	በቁጥር	600

1.3. የአርክቴክትስ ወርሃዊን ማስቀጠል		
ዝግጅት	በቁጥር	6
1.4. የማሕበሩን ውክልና እና ተደራሽነት ማሳደግ		
	በፐርሰንት	100
1.5. ገቢን ማሳደግ		
ጠቅላላ	በቁጥር	8,000,000
የአባላት ክፍያ	በቁጥር	1,200,000
ሆነራሪየም	በቁጥር	3,800,000
ስፖንሰር	በቁጥር	3,000,000
1.6. አለማቀፍ ግንኙነነቶችን ማጠናከር		
የአለም አቀፉን አመታዊ መዋጮ መክፈል	በቁጥር	1
ከአፍሪካ አርክቴክቶች ማሕበር ጋር ስምምነት መድረስ እና መዋጮ መክፈል	በቁጥር	1
ቢያንስ ከሶስት አለም አቀፍ ተቋማት ጋር ስራ መስራት	በቁጥር	3
1.7. የተለያዩ ስልጠናዎችን ማመቻቸት		
	በቁጥር	3
1.8. የአርክቴክቶች ሕግ ማእቀፍን ማዘጋጀት		
አርታኦት ኮሚቴ ማደራጀት	በፐርሰንት	1
ባለድርሻ አካላት ውይይት	በቁጥር	2